ኅብረት ለምርጫ(CECOE)
የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ኅብረት ለምርጫ
Coalition of Ethiopian Civil Society
Organizations for Elections


# የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ሰብሳቢ የዕጩዎች ጥቆማ፣ አመራረጥ እና ሹመት ሂደት የክትትል ሪፖርት


ጥር 2016
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

# ማውጫ


| | |
|---|---|
| መግቢያ | 1 |
| ዳራ | 2 |
| የብሔራዊ ምርጫ ቦርድን የሚያቋቁመው ማዕቀፍ | 5 |
| የዕጩዎች ጥቆማ፣ አመራረጥ እና ሹመት ሂደት ከሕግ እና ከዴሞክራሲ መርሆዎች አኳያ | 7 |
| ማጠቃለያ | 10 |

# መግቢያ

የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ኅብረት ለምርጫ (ኅብረት ለምርጫ) በ2011 የተቋቋመ ሲሆን የሲቪል ማህበራት በምርጫ ትዝብት ፣ ክትትል፣ የመራጮች ትምህርት እና ከምርጫ በኋላ ግጭቶችን በመከላከል ላይ ያላቸውን ሚና ለማሳደግ እና ለማስተባበር የተቋቋመ ነው። ኅብረት ለምርጫ በተመሰረተ ማግስት የሲዳማ ህዝበ ውሳኔን በተቀናጀ መልኩ በመታዘብ በኢትዮጵያ የሲቪል ማህበራት ዘርፍ ውስጥ አዲስ ምዕራፍን ከፍቷል። ይህንን ልምድ በመቀመር በስድስተኛው የኢትዮጵያ ብሔራዊ እና ክልላዊ ምርጫ ኅብረት ለምርጫ ከ3,500 በላይ የረጅም ጊዜ እና የአጭር ጊዜ ታዛቢዎችን በዘጠኝ ክልሎች እና ሁለት ከተማ አስተዳደሮች መልምሎ በማሰልጠን አሰማርቷል። ይህም ሰኔ 2013 ዓ.ም እና መስከረም 2014 ዓ.ም በተካሄደው ስድስተኛው ጠቅላላ ምርጫ እና በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝበ ውሳኔ የተካሄዱትን ምርጫዎች ያካትታል። በመቀጠልም በጥር ወር 2015 ዓ.ም በደቡብ ክልል ስድስት ዞኖች እና አምስት ልዩ ወረዳዎች የተካሄደውን ህዝበ ውሳኔ እና በሰኔ 19 ቀን 2015 ዓ.ም የተካሄደውን የወላይታ ዞን ድጋሚ ህዝበ ውሳኔ በተሳካ ሁኔታ ታዝቧል።

የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድን እና አዲስ የምርጫ ቦርድ ሰብሳቢ ሹመትን ወሳኝነት በመገንዘብ ኅብረቱ የምርጫ ቦርድን ሰብሳቢ የአመላመል እና ሹመት ሂደት በቅርበት ተከታትሏል። ይህ የግምገማ ሪፖርት የምርጫ ቦርድ ሰብሳቢን ምልመላ፣ አመራረጥ እና የሹመት ሂደት እንዲሁም ሂደቱ ሕጉን የተከተለ ስለመሆኑ በሚዲያ የወጡ ሪፖርቶች እና መልማይ ኮሚቴው በሰጣቸው ጋዜጣዊ መግለጫዎች ላይ በመመስረት በዝርዝር ፈትሿል። ሪፖርቱ እንደ ግልፅነት፣ አካታችነት እና አሳታፊነት ያሉ ዋና ዋና የፖለቲካ ሂደትን መመዘኛዎችን በመጠቀም ለወደፊት ለሚከናወኑ የአሿሿም ሂደት ለማሻሻል ምክረ-ሃሳቦች ለመስጠት ሞክሯል። ይህም የዲሞክራሲያዊ መርሆዎችን ለማስከበር፣ ዜጎች በምርጫ ሥርዓቱ ላይ እምነት እንዲያድርባቸው፣ የምርጫ ቦርድ ሰብሳቢ አመራረጥን በተመለከተ ግልጽና በበቂ መረጃ ላይ የተመሰረተ ውይይት ለማድረግ የበኩሉን አስተዋጽዖ በማበርከት፣ በኢትዮጵያ የሚካሄዱ ምርጫዎች ተዓማኒነት እና ቅቡልነት ለማረጋገጥ ቁልፍ አስተዋጽዖ ይኖረዋል።

# ዳራ

የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 102 የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድን (ምርጫ ቦርድ) ነፃ እና ገለልተኛ የምርጫ አስተዳደር አካል አድርጎ አቋቁሟል። በአዋጅ ቁጥር 1133/2011 በድጋሚ የተቋቋመው እና ምርጫዎችን የማስፈጸም ስልጣን የተሰጠው ቦርዱ ህጉን በጠበቀ መልኩ የፖለቲካ ፓርቲዎችን የመመዝገብ እና የመቆጣጠር ኃላፊነቶችን እንዲሁም በየደረጃው የሚደረጉ ምርጫዎች ነፃ እና ፍትሃዊ በሆነ መንገድ እንዲካሄዱ ያደርጋል።

የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) አስተዳደር ወደስልጣን ከመጣ አንስቶ በርካታ ጉልህ የማሻሻያ እርምጃዎችን የወሰደ ሲሆን ከእነዚህም አንዱ ከኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ጋር የተያያዘ ነው። በዚህም መሰረት ምርጫ ቦርድ ራሱን የቻለ፣ ነፃ እና ገለልተኛ አካል ተጠሪነቱም ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሆኖ በአዋጅ ቁጥር 1133/2011 ተቋቁሟል። በተጨማሪም አዲስ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ እና የምርጫ ሥነ-ምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011ን በማውጣት በምርጫ እና በፖለቲካ ፓርቲዎች አስተዳደር ላይ ተጨባጭ ማሻሻያዎችን ለማከናወን ጥረቶች ሲደረጉ ቆይተዋል።

ከዚህ በተጨማሪ ብርቱኳን ሚደቅሳ ህዳር 2011 ዓ.ም የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሰብሳቢ ሆነው መሾማቸው ከለውጡ በፊት ከነበራቸው የፖለቲካ ተሳትፎ ታሪክ አንፃር፣ በሕዝብ፣ በፖለቲካ ፓርቲዎች፣ በሲቪል ማኅበራት እንዲሁም በልማት እና በዓለም አቀፍ አጋሮች ዓይን በኢትዮጵያ የምርጫ ስርዓት እና የዲሞክራሲ ግንባታ ላይ ተዳክሞ የቆየውን እምነት የማደስ አቅም ነበረው።

*ብርቱካን ሚደቅሳ(በስተቀኝ) የቀድሞ ምርጫ ቦርድ ሰብሳቢ ሲሾሙ (ጥቅምት 2011) (ፎቶ፡ ፋና)*



ኢትዮጵያ በፖለቲካ አለመረጋጋት፣ በግጭት እና በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ውስጥ ባለችበት አስቸጋሪ ወቅት እንደ አዲስ የተቋቋመው ቦርድ ነፃ፣ ፍትሃዊ፣ ግልጽ፣ ተጠያቂነት ያለው እና አካታች ምርጫን ማካሄድን ጨምሮ ለሂደቱ አስፈላጊ የሆኑ የሕግ እና የተቋም ማሻሻያዎችን የማከናወን ኃላፊነቶች ተጥለውበት ነበር። በእነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ በብርቱኳን ሚደቅሳ አመራር ሰጪነት ቦርዱ የሲዳማ ህዝበ ውሳኔን፣ ስድስተኛው ጠቅላላ ምርጫን፣ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝበ ውሳኔን እና የደቡብ ኢትዮጵያ ህዝበ ውሳኔን ለማስፈጸም ችሏል።

ሰኔ 2015 ዓ.ም፤ የምርጫ ቦርድን ለአራት (4) ዓመታት ሲመሩ የቆዩት ሰብሳቢዋ ከነሐሴ 07 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ ኃላፊነታውን መልቀቃቸውን አስታውቀዋል። ይህን ተከትሎም ህዳር 6 ቀን 2016 ዓ.ም ጠቅላይ ሚኒስትሩ የምርጫ ቦርድ ሰብሳቢን ለመሾም ስምንት (8) አባላት ያሉት የምልመላ ኮሚቴን ማቋቋማቸውን አስታውቀዋል። ኮሚቴው በሚከተሉት የተቋማት ተወካዮች የተዋቀረ ነበር።

1. *ቄስ ታጋይ ታደለ - ሊቀ መንበር - የኢትዮጵያ የኃይማኖቶች ጉባኤን በመወከል፣*
2. *ተከተል ዮሃንስ - አባል - የኢትዮጵያ ሳይንስ አካዳሚ ተወካይ፣*
3. *ካሳሁን ፎሎ - አባል - የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማህበራት ኮንፌዴሬሽን በመወከል፣*
4. *መላኩ አዘዘው - አባል - የኢትዮጵያ የንግድ እና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤትን በመወከል፣*
5. *ርግበ ገብረሃዋርያ- አባል - የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽንን በመወከል፣*
6. *ባዩህ በዛብህ - አባል - የሲቪል ማህበራትን የሚወክል፣*
7. *ዮሃንስ በንቲ (ዶ/ር) - አባል - የሲቪል ማህበራትን የሚወክል፣*
8. *እንግዳዬ እሸቴ አባል - የሲቪል ማህበራትን የሚወክል።*

የምርጫ ቦርድ ሰብሳቢን ለመተካት ዕጩዎችን ለመመልመል የተቋቋመው ኮሚቴ ከህዝብ፣ ከፖለቲካ ድርጅቶች እና ከሲቪል ማህበራት በሚቀርቡ ጥቆማዎች ለምርጫ ቦርድ ሰብሳቢነት ብቁ ዕጩዎችን ከሕዝብ ሰብስቦ፤ በመለየት እና ፈቃደኝነታቸውን በማረጋገጥ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዲያቀርብ ኃላፊነት ተሰጥቶታል።

ኮሚቴው አርብ ህዳር 10 ቀን 2016 ዓ.ም በሰጠው መግለጫ ከሰኞ ህዳር 13 ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ ለ10 ተከታታይ ቀናት ዕጩዎችን መቀበል እንደሚጀምር በሰብሳቢው ታጋይ ታደለ (ቀሲስ) አማካኝነት ገልጿል።[1] ሰብሳቢው በሰጡት መግለጫ፣ ኮሚቴው የውስጥ አሰራር መመሪያ እና የሥራ መርሃ ግብር ማውጣቱ ተጠቅሷል። በሕዝብ፣ በፖለቲካ ድርጅቶችና በሲቪል ማኅበራት የሚጠቆሙት ዕጩዎች በአዋጅ ቁጥር 1133/2011 አንቀጽ 6 የተዘረዘሩትን ሁሉንም መስፈርቶች ማሟላት እንዳለባቸውም ጠቁመዋል።

ኮሚቴው የተመረጡትን ሁለቱን ዕጩዎችም ከታህሳስ ወር መጨረሻ በፊት ለጠቅላይ ሚኒስትር ዐብይ አህመድ (ዶ/ር) እንደሚያቀርብ አስታውቆ ነበር። ጥቆማዎች እንዴት እንደሚቀርቡም አብራርተዋል። በመግለጫው መሰረት ጥቆማዎች በኮሚቴው በተዘጋጀው ቅጽ የዕጩዎችን ማንነት እና ሌሎች መረጃዎችን በመሙላት በኢሜይል፣ በዋትስአፕ፣ በቴሌግራም ወይም በፖስታ ለኮሚቴው መላክ እንደሚቻል ገልፀዋል። ጥቆማዎችን በአካል ቀርበው ማቅረብ የሚፈልጉ በአዲስ አበባ ከተማ አራት ኪሎ በሚገኘው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ዋና ፅህፈት ቤት በተዘጋጀ ዝግ ሳጥን ውስጥ ማስገባት እንደሚችሉም ተገልጿል። ጥቆማዎችን የማቅረቢያ ቀነ-ገደብ ሐሙስ፣ ህዳር 23 ቀን 2016 ዓ.ም ከሰዓት በ11 ሰዓት ተኩል እንደሆነ ተቀምጧል።

1 https://ethiopiainsider.com/2023/12098/

*ሜላትወርቅ ኃይሉ(በስተግራ) የምርጫ ቦርድ ሰብሳቢ ሆነው ሲሾሙ(ታህሳስ 2016), (ፎቶ: HoPR/Facebook)*



የመጀመሪያ መግለጫውን ከሰጠ ከ22 ቀናት በኋላ ታህሳስ 2 ቀን 2016 ዓ.ም የምርጫ ቦርድ ሰብሳቢ ዕጩዎችን በተመለከተ የምልመላ ኮሚቴው ሁለተኛውን ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጥቷል። ከህዳር 13 ቀን እስከ ህዳር 23 ቀን 2016 ዓ.ም በቆየው የዕጩዎች ማቅረቢያ ጊዜ በአጠቃላይ 56 ዕጩዎች በተለያዩ መንገዶች እንደተጠቆሙ ኮሚቴው ገልጿል። ኮሚቴው የዕጩዎች ማቅረቢያ ጊዜን ተከትሎ ሶስት ዙሮችን ያካተተ ጥብቅ የአመራረጥ ሂደት ማካሄዱን፤ ዕጩዎችን በጥንቃቄ ገምግሞ አምስት ዕጩዎችን መለየቱን፤ ጥልቅ ውይይት ማድረጉን እና በአዋጁ የተገለፁትን መስፈርቶች ያሚሉ ሁለት ዕጩዎችን ማለትም ወ/ሮ ሜላተወርቅ ኃይሉ እና አቶ ታደሰ ለማ መለየቱን አስታውቋል።

ኮሚቴው ሁለቱ ዕጩዎች የተመረጡት ባላቸው ሪከርድ፤ ከፖለቲካ ወገንተኝነት ነፃ በመሆናቸው እና ሁሉንም አስፈላጊ መስፈርቶች በማሟላታቸው እንደሆነ አጽንዖት ሰጥቷል። ኮሚቴው እንደገለጸው መሰረት የሁለቱን ዕጩዎች ስም ለጠቅላይ ሚኒስትሩ እንደሚያስተላለፍ የጠቅላይ ሚኒስትሩን የውሳኔ ሃሳብ ተከትሎ ከሁለቱ ዕጩዎች መካከል አንዱ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የምርጫ ቦርድ ሰብሳቢ ሆነው እንደሚሾም/ምትሾም ገልጸው ነበር። በዚህም መሰረት ታህሳስ 12 ቀን 2016 ዓ.ም የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ባደረገው መደበኛ ስብሰባ ወይዘሮ ሜላተወርቅ ኃይሉን የምርጫ ቦርድ ሰብሳቢ አድርጎ ሾሟል።

# የብሔራዊ ምርጫ ቦርድን የሚያቋቁመው ማዕቀፍ

በ1995 የወጣው የኢፌዲሪ ህገ መንግስት ብሔራዊ ምርጫ ቦርድን በአንቀፅ 102 አቋቁሟል። ህገ መንግስቱ ይህ አካል ከማንኛውም ተጽእኖ ነፃ በመሆን ነፃ እና ፍትሃዊ ምርጫን በፌደራል እና በክልል ደረጃ በገለልተኝነት እንዲያስፈጽም ኃላፊነት ሰጥቶታል። የኢፌዴሪ ህገ መንግስት የቦርድ አባላትን ስያሜና ሹመት ዝርዝር መረጃ ለበታች ህጎች የተወ ሲሆን የቦርድ አባላት በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በጠቅላይ ሚኒስትሩ አቅራቢነት እንደሚሾሙ ይደነግጋል።[2]

በ2011 ዓ.ም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ማቋቋሚያ በአዋጅ ቁጥር 1133/2011 መሰረት ራሱን የቻለ ሕጋዊ ሰውነት ያለው አካል ሆኖ እንደገና ተቋቁሟል።[3] የምርጫ ቦርድ ስልጣን አጠቃላይ ምርጫዎችን እና ህዝበ ውሳኔዎችን ማስፈጸምን የሚያካትት ሲሆን በአዋጁ በተገለፀው መሰረት የተለያዩ ሥልጣንና ኃላፊነቶች ተሰጥተውታል።[4] እነዚህም በምርጫ ህጉ መሰረት ምርጫ እና ህዝበ ውሳኔን በገለልተኝነት ማስፈፀም፣ የፖለቲካ ፓርቲዎችን መመዝገብ እና ቁጥጥር ማድረግ፣ ምርጫዎች በየደረጃው በነጻና በፍትሃዊ መንገድ እንዲካሄዱ ማድረግ እና ሌሎችም ይገኙበታል።[5] ምርጫ ቦርድ አምስት አባላትን ባቀፈ የማኔጅመንት ቦርድ የሚተዳደር ሲሆን ሰባሳቢው የተለያዩ የቦርዱን የሥራ ክፍሎችን ይመራል።[6]

በአዋጅ ቁጥር 1133/2011 መሰረት ጠቅላይ ሚኒስትሩ የስራ አመራር ቦርድ ዕጩዎችን የሚመለምል ከላይ የተዘረዘሩት ተቋማት ተወካዮችን ያቀፈ ገለልተኛ ኮሚቴ የማቋቋም ኃላፊነት አለባቸው። [7] በአጠቃላይ ኮሚቴው ስምንት(8) አባላትን ያቀፈ ሲሆን በምልመላ ሂደቱ ውስጥ ተመጣጣኝ የፆታ ተዋፅዖ ሊኖረው እንደሚገባ በአዋጁ ላይ ተደንግጓል። በአዋጁ አንቀጽ 5(2) መሰረት "በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ስር ለተዘረዘሩት ተቋማት የሚወከሉት ወይም የሚመረጡት የኮሚቴ አባላት ገለልተኛነታቸውና ብቃታቸው የተረጋገጠ፣ እንደአግባብነቱ በአንቀጽ 6 ስር የተዘረዘሩትን የሥራ አመራር ቦርድ አባልነት መስፈርቶች የሚያሟሉ እና የኮሚቲው ስብጥር ተመጣጣኝ የጾታ ተዋጽዖ ያለበት" ሊሆን እንደሚገባው ይገልፃል። [8]

2 የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 102
3 አዋጅ ቁ. 1133/2019 አንቀጽ 3
4 አዋጅ ቁ. 1133/2019 አንቀጽ 7 እና 8
5 ዝኒ ከማሁ
6 አዋጅ ቁ. 1133/2019 አንቀጽ 4
7 አዋጅ ቁ. 1133/2019 አንቀጽ 5
8 ዝኒ ከማሁ

ኮሚቴው ለቦርድ አባልነት ከህዝብ፣ ከፖለቲካ ድርጅቶች እና ከሲቪል ማህበራት ዕጩዎችን የመቀበል ኃላፊነት አለበት።[9] ግልጽ እና ፉክክር በተሞላበት ሂደት ኮሚቴው ለሥራ አመራር ቦርድ ብቁ የሆኑ ዕጩዎችን መምረጥና የዕጩዎቹ ፈቃድ መኖሩንም ያረጋግጣል። ኮሚቴው የዕጩዎችን ዝርዝር በማዘጋጀት ለህዝብ ይፋ ተደርጎ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ይልካል።[10] የዕጩዎች ዝርዝር በቦርዱ ውስጥ ካሉት የሥራ መደቦች ብዛት እጥፍ መሆን አለበት።[11]

በመቀጠልም ጠቅላይ ሚኒስትሩ የቀረቡትን ዕጩዎች በተመለከተ ከተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች ተወካዮች ጋር ምክክር ማድረግ አለባቸው። ከምክክሩ ሂደት በኋላ ጠቅላይ ሚኒስትሩ የመረጡትን ዕጩ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያቀርባሉ። በዚህ ሂደት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሁለቱም የሥራ መደቦች ክፍት ከሆኑ የሥራ አመራር ቦርዱን ሊቀመንበር እና ምክትል ሊቀመንበር ይለያሉ። ዕጩዎቹ የሚሾሙት በህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ቀርበው በድምጽ ብልጫ ይሁንታ ሲያገኙ ነው።

ከሹመቱ አሠጣጥ ሂደት በተጨማሪ የማኔጅመንት ቦርድ አባል ለመሆን የሚፈልጉ ግለሰቦች ሊያሟሏቸው የሚገቡ መስፈርቶች አሉ። እነዚህ መመዘኛዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፤

1. በትውልድ ኢትዮጵያዊ የሆነ/ች ኢትዮጵያዊ ዜጋ፣
2. የማንኛውም ፖለቲካ ድርጅት አባል ያልሆነ/ች፣
3. ከምርጫ ጉዳዮች ጋር ተያያዥነት ባላቸው አካባቢዎች በተለይም በህግ፣ በፖለቲካል ሳይንስ፣ በህዝብ አስተዳደር፣ በስታቲስቲክስ፣ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እና ሌሎች ተዛማጅነት ባላቸው ዘርፎች ከፍተኛ ሙያዊ ብቃት ያለው/ያላት፣
4. መልካም ሥነ-ምግባር እና ስብዕና ያለው/ላት፣
5. የተሰጠውን/ጣትን ኃላፊነት ለመሸከም የሚያስችል ከፍተኛ የአመራር ብቃት ያለው/ላት፣

በተጨማሪም የማኔጅመንት ቦርድ ስብጥር የብሄር እና የፆታ ተዋፅዖን ከግምት ውስጥ በማስገባት የተለያዩ ብሄረሰቦች እና ጾታዎች ሚዛናዊ ውክልና እንዲኖራቸው ማድረግ እንዳለበት አዋጁ ይደነግጋል።

---

9 ዝኒ ከማሁ፣ንዑስ አንቀጽ 3

10 ዝኒ ከማሁ፣ ንዑስ አንቀጽ 5

11 ዝኒ ከማሁ፣ንዑስ አንቀጽ 6

# የዕጩዎች ጥቆማ፣ አመራረጥ እና ሹመት ሂደት ከሕግ እና ከዴሞክራሲ መርሆዎች አኳያ

## ግልጽነት

ግልጽነት ለማንኛውም የፖለቲካ ሂደት ተዓማኒነት፣ ፍትሃዊነት እና ተጠያቂነት መሰረታዊ መርህ ነው። በዚህ አግባብ ግልጽነት በመላው ሂደት ሊኖር የሚገባውን የመረጃ እና የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ክፍት መሆንን እንዲሁም መረጃዎች በቀላሉ መገኘት መቻላቸውን ይመለከታል። ዕጩዎችን የሚመለምለው በምርጫ ህጉ የተመሰረተ ኮሚቴ በጠቅላይ ሚኒስትሩ መቋቋሙ፣ የዕጩዎች መመልመያ የጊዜ ሰሌዳ ለህዝብ ይፋ መደረጉ እና በመልማይ ኮሚቴው የተመረጡ ሁለት (2) ዕጩዎች ለህዝብ ይፋ መደረጋቸው እነዚህ ሂደት ከግልጽነት መርህ ጋር የሚስማሙ እንደነበሩ ማሳያ ናቸው። ሆኖም ግን፣ በምልመላ፣ የአመራረጥ እና የሹመት ሂደት ላይ የተስተዋሉ ሊሻሻሉ የሚገባቸው ጉዳዮች አሉ።

ምንም እንኳ ኮሚቴው ምልመላውን ለማከናወን የተለያዩ የምልመላ ዘዴዎችን በመጠቀም ጥቆማ ማቅረብ እንደሚቻል ይፋ ቢያደርግም፣ ኅብረት ለምርጫ ባደረገው ውስን ምልከታ በተግባር ላይ የዋሉት የምልመላ ዘዴዎች ዕጩዎችን ለጠቆሙ ዜጎች ጥቆማቸው በተሳካ ሁኔታ መድረሱን የሚገልጽ ማረጋገጫ አልሰጡም። በተጨማሪም በአካል የሚደረጉ ጥቆማዎች በሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ቢሮ በመገኘት ብቻ መሆኑ በሩቅ አካባቢዎች የሚኖሩና ጥቆማ ማድረግ የሚፈልጉ ዜጎች አዳጋች ያደርገዋል።

ዕጩዎችን የመለየት እና የአመራረጥ ሂደት ግልጽነት የጎደላቸው እና ማብራሪያ የሚፈልጉ ነበሩ። ኮሚቴው እያከናወናቸው የነበሩ ሥራዎች በየጊዜው ማብራሪያ አለመስጠቱ እንዲሁም ስለተጠቆሙ ዕጩዎች ማንነት ገለፃ አለማድረጉ በ2011 ዓ.ም ተደርጎ ከነበረው የምርጫ ቦርድ አባላት አመራረጥ ሂደት ላይ ከነበረው የመረጃ አቅርቦት አኳያ ሲታይ ክፍተቶች እንዳሉ ማስተዋል ተችሏል። በየወቅቱ የሚደረጉ ማብራሪያዎች እና ገለጻዎች የሂደቱን ግልጽነት ከማረጋገጥ አኳያ ለዜጎች መረጃዎችን በበቂ ለማቅረብ ትልቅ ሚና ይጫወታሉ።

እነዚህን ታሳቢ በማድረግ ኅብረት ለምርጫ የሚከተሉትን ከግልጽነት ጋር የተገናኙ ምክረ-ሃሳቦች ወደፊት ለሚደረጉ ተመሳሳይ የምርጫ ቦርድ የሥራ አመራር ቦርድ አባላት አመራረጥ ሂደት እንዲሻሻሉ ያቀርባል፡-

1. የጥቆማ አቅራረብ ሂደቱን ተደራሽነት የሚያሳድጉ እንዲሁም በጥቅም ላይ የሚውሉ የዕጩዎች ጥቆማ ማቅረቢያ ዘዴዎችን ሕዝብ እንዲያውቃቸው የተለያዩ ሥራዎች ሊሰሩ ይገባል። ይህም ዕጩዎችን የሚጠቁሙ ዜጎች በተሳካ ሁኔታ ጥቆማ ሲያቀርቡ የማረጋገጫ መልዕክት እንዲደርሳቸው ማድረግን ያካትታል። በተጨማሪም፣ ኮሚቴው በክልሎች ደረጃ በአካል ለሚደረጉ ጥቆማዎች መቀበያ ቦታዎችን ሊያመቻች ይገባል።
2. ኮሚቴው እያከናወናቸው ስላሉ እንቅስቃሴዎች እንዲሁም እየተደረጉ ባሉ ጥቆማዎች ላይ በየጊዜው ማብራሪያ እና ገለጻ ሊሰጥ ይገባል።
3. የተጠቋሚዎችን ሥም ዝርዝር እና ሌሎች መረጃዎችን ለሕዝብ ይፋ በማድረግ በጥቆማ ውስጥ የተሳተፉ አካላት የጠቆሚቸው ግለሰቦች በዕጩዎች ልየታ ሂደቱ ውስጥ መካተታቸውን እንዲከታተሉ እና እንዲያረጋግጡ ማድረግ ይቻላል።

# አካታችነት

አካታችነት በማንኛውም ዕጩዎችን በመጠቆም፣ በመመልመል እና በመምረጥ ሂደት ውስጥ መሟላት ያለበት እጅግ አስፈላጊ መርህ ነው። ይህ መርህ እንደ ኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ያሉ የምርጫ አስተዳደር አካልን የሚመሩ ግለሰቦች በሚመረጡበት ወቅት እነዚህ አመራር አካላት የአካታችነት መርህን በስፋት በምርጫ ሥርዓቱ ላይ የመተግበር ኃላፊነት ስለሚጣልባቸው አስፈላጊነቱ የላቀ ይሆናል።

ይህንን ታሳቢ በማድረግ አዋጁ የአካታችነት መርህ በተለይም ከጾታ፣ እንዲሁም ከብሔር አኳያ በዕጩዎች ጥቆማ፣ አመራረጥ እና ሹመት ሂደት ውስጥ እንዲካተት ደንግጓል። የምልመላ ኮሚቴው በሚዋቀርበት ወቅት የጾታ ተመጣጣኝነት ታሳቢ እንዲደረግ አዋጁ ያስቀምጣል። ስምንት አባላት ያሉትን ኮሚቴ የፆታ ስብጥር ስንመለከት የሴቶች ድርሻ ሁለት ብቻ ሆኖ እናገኘዋለን። እነዚህ ሴት የኮሚቴው አባላት ተወክለው የመጡት ከኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን እና አንድ ስሙ ካልተገለጸ የሲቪል ማህበር ድርጅት ነው።[12] ይህ በኮሚቴው ያለው የሁለት ለስድስት የጾታ ምጣኔ (ሁለት ሴት እና ስድስት ወንድ) አዋጁ ከሚያስቀምጠው የጾታ ተመጣጣኝነት ድንጋጌ አኳያ አብሮ የሚሄድ ባይሆንም እነዚህን ሁለት ሴት የኮሚቴ አባላት የወከሉትን ድርጅቶች የሚያስመሰግን ነው። በሌላ በኩል አዋጁ አካል ጉዳተኞችን ለማካተት የሚያስችል ድንጋጌ ባለማስፈሩ ከአካታችነት መርህ ጋር የሚጣጣም አይደለም። ይህም አዋጁ በኮሚቴው ውስጥ የሚካተቱ አካላትን አመራረጥ የጾታ ተመጣጣኝነትን ታሳቢ ያደረገ ቢሆንም የአካል ጉዳተኞችን ተሳትፎ ግን አለማካተቱ በኮሚቴው ውስጥ የአካል ጉዳተኞች ተሳትፎ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሯል።

በተጨማሪም ከሕዝብ የተደረገው የዕጩዎች ጥቆማ በአጠቃላይ የተላኩ 56 ጥቆማዎች ውስጥ አራት (4) ሴት ዕጩዎችን ብቻ መሆናቸው ከሕዝብ የደረሱ ጥቆማዎች ከፍተኛ የጾታ አለመመጣጠን እንደነበረባቸው ያሳያል።

እነዚህን ታሳቢ በማድረግ ኅብረት ለምርጫ የሚከተሉትን ከአካታችነት ጋር የተገናኙ ምክረ-ሃሳቦች ወደፊት ለሚደረጉ ተመሳሳይ የምርጫ ቦርድ የሥራ አመራር ቦርድ አባላት አመራረጥ ሂደት እንዲሻሻሉ ያቀርባል፦

1. ኅብረት ለምርጫ ሴት ወኪሎችን ለኮሚቴው የላኩ ድርጅቶችን ማለትም የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽንና በስም ያልተጠቀሰ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅትን እያመሰገነ ሌሎቹ የኮሚቴው አባል ድርጅቶች አካታችነትን በተመለከተ የሁለቱን ድርጅቶችን ልምድ እንዲወስዱ ያበረታታል፤
2. በብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የሥራ አመራር ቦርድ አባላት ጥቆማ አሰጣጥ፣ አመራረጥ እና አሿሿም ሂደት ላይ የአካል ጉዳተኞችን ተሳትፎ ታሳቢ በማድረግ በአስመራጭ ኮሚቴው ውስጥ በአካል ጉዳተኞች ላይ የሚሰራ ድርጅት እንዲካተት አዋጁ ላይ ማሻሻያ እንዲደረግ ኅብረት ለምርጫ ሀሳብ ያቀርባል፤

12 ወ/ሮ ሪግበ ገብረሃዋርያ ከኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን (ኢሰመኮ) እና እንግዳዬ እሸቴ ከሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ተወክለዋል፡

3. ከአጠቃላይ 56 ተጠቋሚዎች መካከል አራቱ (4) ብቻ ሴቶች መሆናቸው፤ በሂደቱ ላይ የነበረውን ዝቅተኛ የሆነ የሴቶች ጥቆማ ያሳያል። ይህን ሁኔታ ለማሻሻል የሚመለከታቸው አካላት በተለይም በሴቶች መብቶች ላይ አተኩረው የሚሰሩ ድርጅቶችና ተቋማት በአዋጁ የተዘረዘሩ መስፈርቶችን የሚያሟሉ ሴቶች እንዲጠቆሙ የተለያዩ ሥራዎችን እንዲያከናውኑ ያሳስባል።

# አሳታፊነት

በማንኛውም የምርጫ ሂደት ውስጥ የሚመለከታቸው አካላትን ሁሉ ማሳተፍ ወሳኝነት አለው። የአሳታፊነት መርህ እንደቡድን ወይም ግለሰብ የህዝብን ተሳትፎ የሚያካትት በመሆኑ ብዙ እንድምታ ያለው መርህ ነው። በህዝብ ጉዳይ ላይ ያለውን ጠቀሜታ ከግምት ውስጥ በማስገባት በተለይም የምርጫ አስተዳደር አካልን የሚመሩ ግለሰቦች አመራረጥ ዜጎችን፣ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን፣ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ቡድኖችን፣ የፖለቲካ ፓርቲዎችን እና ሌሎች ባለድርሻ አካላትን ባሳተፈ መልኩ ሊከናወን ይገባል። እነዚህን መርሆዎች ታሳቢ በማድረግ አዋጅ ቁጥር 1133/2011 አስፈላጊ የሚባሉ የተሳትፎ ጉዳዮችን በዕጩዎች አጠቋቆም፣ አመራረጥ፤ እና አሿሿም ሂደት ውስጥ አካቷል። በዚህም መሰረት አዋጁ አምስት መቀመጫዎችን በስም ለተዘረዘሩ ድርጅቶች እና ሶስት መቀመጫዎችን ደግሞ፤ ለሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች እና ለአገር ሽማግሌዎች ደልድሏል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ የቦርዱን ሰብሳቢ እንዲያስመርጥ ያቋቋሙት ኮሚቴ በአዋጁ አንቀጽ 5 በተቀመጡት ድንጋጌዎች መሰረት ሲሆን ይህ የተቋቋመው ኮሚቴ በተወሰነ የጊዜ-ገደብ የዕጩዎች ጥቆማ እንዲቀርብ ለህዝብ ጥሪ አድርጓል። ከዚህ በተጨማሪም ኮሚቴው መርጦ በሚልክላቸው ዕጩዎች ዝርዝር ላይ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር እንዲማከሩ የሚጠይቀው የአዋጁ አንቀጽ 5(6) ቢኖርም እንኳን ጠቅላይ ሚኒስትሩ በኮሚቴ ተለይተው በተላኩላቸው ዕጩዎች ላይ ከፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር ውይይት አለማድረጋቸውን የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ሠብሳቢ ገልጸዋል።[13]

እነዚህን ታሳቢ በማድረግ ኅብረት ለምርጫ የሚከተሉትን ከአካታችነት ጋር የተገናኙ ምክረ-ሃሳብ ወደፊት ለሚደረጉ ተመሳሳይ የምርጫ ቦርድ የሥራ አመራር ቦርድ አባላት አመራረጥ ሂደት እንዲሻሻሉ ያቀርባል፡-

1. ኮሚቴው ጥቆማ አቅራቢዎች በሂደቱ በንቃት እንዲሳተፉ ለማስቻል ለጥቆማ ሰፋ ያለ ጊዜ መስጠት ይኖርበታል፤
2. በጥቆማ አሰጣጥ ሂደቱ ውስጥ ግልፅነትን እና የህዝብ ተሳትፎን ለማጎልበት አዋጁ አስመራጭ ኮሚቴው የሚመርጣቸው ዕጩዎች ላይ የህዝብ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች እና የሲቪል ማህበረሰቦች ያላቸውን ሃሳብ እና አስተያየት እንዲሰጡ የሚያስችሉ የተለያዩ መድረኮችን እንዲያመቻች የሚያስገድድ የህግ ድንጋጌ በአዋጁ ውስጥ ማካተት ይኖርበታል፤
3. በአዋጁ መሰረት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ቀጣይ በሚደረጉ ተመሳሳይ ሂደት ከኮሚቴው በሚቀርቡላቸው ዕጩዎች ላይ ከፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር እንዲማከሩ ኅብረት ለምርጫ ምክረ-ሃሳቡን ያቀርባል፤
4. የሲቪል ማህበራት መስፈርቱን የሚያሟሉ ዕጩዎችን በመጠቆም እና ሕዝቡ በጥቆማ ሂደቱ በንቃት እንዲሳተፍ እንዲያበረታቱ ኅብረት ለምርጫ ይመክራል።

13 "በጠቅላይ ሚኒስትሩ አቅራቢነት የተሰጠው የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሰብሳቢ ሹመት የሕግ ጥሰት አለበት ተባለ", ሪፖርተር - Ethiopian Reporter - Available at: https://ethiopianreporter.com/125115/ (Accessed on January 9, 2024).

# መደምደሚያ

የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ሰብሳቢን በአጭር ጊዜ ለመተካት የተደረገው ጥረት ይበል የሚያሰኝ ቢሆንም ህብረቱ በተካሄደው የሹመት ሂደት ላይ መሻሻል የሚገባቸው የሚከተሉትን ጉዳዮች አስተውሏል።

- **ግልጽነትን ከማረጋገጥ አንፃር** የኮሚቴው አወቃቀር እና ዕጩዎችን የመጠቆሚያ ጊዜ እና መንገድ ይፋ የተደረጉ ቢሆንም ሌሎች መረጃዎች ግን በበቂ ሁኔታ ይፋ አልተደረጉም ነበር። በሂደቱ መረጃን ለሕዝብ በበቂ ሁኔታ አለመድረሱ ለተለያዩ መላምቶች በር ይከፍታል።

- **አካታችነትን ከማረጋገጥ አንፃር** በኮሚቴው ውስጥ ተመጣጣኝ የሴቶች ቁጥር አለመኖሩ፤ እንዲሁም አካል ጉዳተኞች ለማካተት የሚያስችል አስገዳጅ የህግ ድንጋጌ አለመኖሩ፤ ከተጠቆሙ 56 ዕጩዎች መካከል የሴቶች ቁጥር አራት ብቻ መሆኑ፤

- **አሳታፊነትን ከማረጋገጥ አንፃር** ሕዝብ በዕጩዎች ጥቆማ እንዲሳተፍ እድሉን ለማመቻቸት የተሞከረ ቢሆንም ለጥቆማ የተሰጠው ጊዜ አጭር መሆን፤በሂደቱ ላይ ሕዝብ ሃሳብ፣ አስተያየት ወይንም ቅሬታ የሚያቀርብበት መድረክ አለመዘጋጀቱ ተሰተዉሏል።

ጥር 2016 ዓም

አዲስ አበባ

የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ኅብረት ለምርጫ (ኅብረት ለምርጫ)

ኅብረት ለምርጫ(CECOE)

የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ኅብረት ለምርጫ

Coalition of Ethiopian Civil Society Organizations for Elections


**የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ኅብረት ለምርጫ (ኅብረት ለምርጫ)**

ሲዲስት ኪሎ፣ አንጎላ መንገድ፣ ሊደር ሺፕ ኢኒስቲውት ሕንጻ፣ 2ኛ ፎቅ
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

+251 11 811 1455
www.cecoe.org
info@cecoe.org
twitter/facebook: @cecoeEth